የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፲፬
አዲስ አበባ—ኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 14
ADDIS ABABA - 24th Nov., 1998

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፯/፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
የማዳበሪያ ማምረትና ንግድ አዋጅ .............. ገጽ ፰፻፺፱

## CONTENTS

Proclamation No. 137/1998
Fertilizer Manufacturing and Trade
Proclamation ...................................... Page 899

### አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፯/፲፱፻፺፩
### የማዳበሪያ ማምረትና ንግድ ድርጅት አዋጅ

የአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት መሠረት የሆነውን ግብርናን በዘመናዊ የእርሻ ሳይንስና በምርት ግብአቶች ማጐልበት በማስ ፈለጉ ፤

ማዳበሪያ ለግብርናው ክፍለ ኢኮኖሚ ወሳኝ ግብአት በመሆኑ ወቅታዊ አቅርቦቱ ፣ ጥራቱን ፣ ግብይቱን ፣ በተፈለገው ቦታና መጠን መሠራጨቱንና መሸጡን በቅርብ መከታተልና ሥርዓት ማስያዝ አስፈላጊ በመሆኑ ፤

ማዳበሪያ ልዩ ጥንቃቄ የሚሻ ኬሚካላዊ ቁስ በመሆኑ በአመራረት ፣ በማስመጣት ፣ በአያያዝና በአከማቻቸት ደረጃውን የጠበቀ ለመሆኑ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ ፤

ማዳበሪያ የሚያመርቱ ፣ የሚያስመጡ ፣ የሚሸጡና የሚያሰራጩ ግለሰቦችን/ድርጅቶችን የሚያግዙ ፣ የሚያማክሩ ፣ የሚቆጣጠሩ መንግሥታዊ አካላትን መሰየም በማስፈለጉ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገመንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

### ክፍል አንድ
### ጠቅላላ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የማዳበሪያ ማምረትና ንግድ አዋጅ ቁጥር ፩፻፴፯/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

### PROCLAMATION NO. 137/1998
### FERTILIZER MANUFACTURING AND TRADE PROCLAMATION

WHEREAS, it is necessary to promote the agricultural sector which is the base of development of the material economy, with modern agricultural science and inputs of manufacture;

WHEREAS, fertilizer is the determining input of the agricultural sector of the economy, it is necessary to follow closely and systematize on time supply, the quality, marketing, distribution and selling of fertilizer to the required quantity;

WHEREAS, fertilizer is a chemical material which needs special care, it is necessary to control and follow up the fertilizer to make sure that it conforms the standard during manufacturing, import, handling and storing;

WHEREAS, it is necessary to appoint governmental bodies which support, advice and control individual organizations engaged in manufacture, import, sale and distribution of fertilizers;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Repulbic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### SECTION ONE
### *General*

1. *Short Title*

This Proclamation may be cited as the "Fertilizer Manufacturing and Trade Proclamation No. 137/1998."

ያንዱ ዋጋ 4.40
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ ፡

፩· "ማዳበሪያ" ማለት ለተክሎች ለምግብነት አስፈላጊ የሆኑትን ንጥረ ነገሮች ለመስጠት አፈር ወይም ተክል ላይ የሚጨመር ካርቦናማ ወይም ካርቦን አልባ የሆነ ሰው ሠራሽ ቁስ ሲሆን ድብልቅን ፤ አካላዊ ድብልቅንና ወደ እንኳርነት የተለወጠ የማዳበሪያ ድብልቅን ይጨምራል ፤ ፍግ ፤ ብስባሽ ፤ አመድ ፤ ጀሶ ፤ ወይም ቆሻሻ በተፈጥሮ ሁኔታቸውና በዚሁ ስማቸው ለንግድ ዓላማ ሲውሉ በዚህ አዋጅ እንደማዳበሪያ ቁስ አይቆጠሩም ፤

፪· "ነጋዴ" ማለት በማዳበሪያ ንግድ ላይ የተሰማራ ማንኛውም ሰው ነው ፡

፫· "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው ፤

፬· "ደረጃ ያላሟላ ማዳበሪያ" ማለት የኢትዮጵያ ደረጃ የጥራት መሥፈርቶችን ያላሟላ ማንኛውም ማዳበሪያ ነው፤

፭· "የማዳበሪያ ንግድ ሥራ" ማለት ማዳበሪያ ፤ የማዳበሪያ ድብልቅ ፤ የማዳበሪያ ልዩ ድብልቅ የማስመጣት ፤ በጅምላ የማከፋፈል ፤ የመቸርቸር ፤ የመላክና የማምረት የንግድ ሥራ ነው ፤

፮· "የተበከለ ማዳበሪያ" ማለት በተክሎች ለምግብነት የሚውሉ የንጥረ ነገር ይዘትን ሊያጠፋ ወይም ሊቀንስ የሚችል ማንኛውም ባዕድ ቁስ የተጨመረበት ማዳበሪያ ነው ፡

፯· "የተነካካ ከረጢት" ማለት ስፌቱ ፤ የእርሳስ እሽጋቱ ወይም ሌላ ቦታ ላይ ተፈትቶ ወይም ተቀድዶ እንደገና በነጋዴው ወይም በሌላ ሰው የተሰፋ ማዳበሪያ የያዘ ከረጢት ነው ፤

፰· "እመዳደብ" ማለት በማዳበሪያ ውስጥ የሚገኝ በመቶኛ የሚገለጽ የተክል ምግብ ይዘት ነው ፤

፱· "አምራች" ማለት ከመጀመሪያው ጥሬ ቁስ ማዳበሪያ ዎችን የሚያመርት ሰው ነው ፤

፲· "የማዳበሪያ ድብልቅ" ማለት የማዳበሪያ አካላዊ ድብልቅና ወደ እንኳርነት የተለወጠ የማዳበሪያ ድብልቅ ነው ፤

፲፩· "የማዳበሪያ አካላዊ ድብልቅ" ማለት በግዑዝ ወይም ያለግዑዝ ቁስ ሁለት ወይም ከሁለት በላይ የሆኑ ማዳበሪያዎችን በአካል በማደባለቅ የሚገኝ የማዳበሪያ ድብልቅ ነው ፤

፲፪· "ወደ እንኳርነት የተለወጠ የማዳበሪያ ድብልቅ" ማለት ማዳበሪያዎችን በሚፈለገው የመጠን ቅንብር በሚገባ በማደባለቅ የሚገኝ የማዳበሪያ ድብልቅ ሲሆን አንድ ላይ ወደ እንኳርነት ሲለወጥ ምንም ዓይነት ኬሚካላዊ አፀግብሮት የማይኖረው ነው ፤

፲፫· "እንኳር" ማለት የተወሰነ የቅንጣት መጠን ያለው ጠጣር (ቆቆር) ማዳበሪያ ማለት ነው ፤

፲፬· "የማዳበሪያ ልዩ ድብልቅ" ማለት ኤጀንሲው መዝግቦ ከያዘው ማዳበሪያ ዓይነት ውጭ ለሙከራ ተግባር የተዘጋጀ ማንኛውም የማዳበሪያ ድብልቅ ነው ፤

፲፭· "ውህድ (ዝንቅ) ማዳበሪያ" ማለት ሁለት ወይም ከሁለት በላይ ንጥረ ነገሮችን የያዘ ማዳበሪያ ሲሆን በሚመረትበት ጊዜ ኬሚካላዊ አፀግብሮት የሚኖረው ነው ፡

2. *Definitions*

Unless the context otherwise requires in this Proclamation:

1) "Fertilizer" means any man made substance organic or inorganic including mixture of fertilizer physical mixture of fertilizer and granulated mixture of fertilizer that is added to the soil or to the plant to supply those elements required in the nutrition of plants manure, compost, ash, gypsum or refuse are not considered as fertilizer materials when they are used for commercial purpose in their original condition and under these names;
2) "Dealer" means any person who is engaged in the business of fertilizer;
3) "Person" means any natural person or juridical organization;
4) "Sub-Standard Fertilizer" means any fertilizer which does not conform to the quality requirements of the Ethiopian standards;
5) "Fertilizer Business" means a business dealing that includes import, wholesale, retail, export and manufacture of fertilizer, mixture of fertilizer and special mixture of fertilizer;
6) "Adulterated Fertilizer" means a fertilizer that contains any foreign substance the addition of which is likely eliminate or decrease the nutrient content of plants;
7) "Tampered Bag" means a bag which contains fertilzer and its stitching, lead sealing or any other place has been broken and stitched again by the dealer or any person;
8) "Grade" means available plant nutrient content in a fertilizer expressed in terms of percentage;
9) "Manufacturer" means a person who produces fertilizer from the original raw material;
10) "Mixture of fertilizer" means a physical mixture of granulated fertilizer;
11) "Physical mixture of fertilizer" means mixture of fertilizers made by physical mixing two or more types of fertilizers with or without inert material;
12) "Granulated mixture of fertilizer" means mixture of fertilizers made by intimately mixing the required amount of fertilizer and granulating them together without involving chemical reaction;
13) "Granule" means a solid fertilizer with the specified particle size;
14) "Special Mixture of Fertilizer" means any mixture of fertilizer, outside of those fertilizers that the Agency hold registering, prepared for experimental purposes;
15) "Composite Fertilizer" means a fertilizer which contains two or more substance and which has a chemical reaction during manufacturing;

፲፮· "አስመጪ እና/ወይም ላኪ" ማለት ማዳበሪያ ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስመጣ እና/ወይም ወደ ውጭ የሚልክ ሰው ነው፡

፲፯· "ኢንስፔክተር" ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፬ መሠረት የተመደበ የማዳበሪያ ኢንስፔክተር ነው ፤

፲፰· "የኢትዮጵያ ደረጃዎች" ማለት በኢትዮጵያ ጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን የተዘጋጁ የማዳበሪያ ደረጃዎች ናቸው ፤

፲፱· "የንግድ ፈቃድ ሰጪ" ማለት እንደአግባቡ የፌዴራል መንግሥት የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ወይም የክልል ወይም ተጠሪነቱ ለፌዴራል መንግሥት የሆነ የከተማ የንግድና ኢንዱስትሪ ቢሮ ወይም ሌላ አግባብ ያለው የፌዴራል ወይም የክልል አካል ነው ፤

፳· "ቦርድ" ማለት እንደአግባቡ የብሔራዊ ማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ ወይም የኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን ቦርድ ነው ፤

፳፩· "ኤጀንሲ" ማለት የብሔራዊ ማዳበሪያ ኢንዱስትሪ ኤጀንሲ ነው ፤

፳፪· "ባለሥልጣን" ማለት የኢትዮጵያ የጥራትና ደረጃዎች ባለሥልጣን ነው ።

፫· የአፈጻጸም ወሰን

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች በማዳበሪያ ንግድ ሥራ በተሠማራ ሰው ላይ ተፈጻሚ ይሆናሉ ።

ክፍል ሁለት

ስለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት

፬· የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አስፈላጊነት

ማንኛውም ሰው በማዳበሪያ ንግድ ሥራ ለመሠማራት ከኤጀንሲው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማውጣት ይኖርበታል ።

፭· በማዳበሪያ የንግድ ሥራ ለመሠማራት የሚያበቁ ሁኔታዎች

፩· ማንኛውም ሰው በማዳበሪያ የንግድ ሥራ ለመሠማራት ኤጀንሲው የሚያወጣቸውን መስፈርቶች አሟልቶ ከኤጀንሲው የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማውጣት ይኖርበታል ።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ ፤

ሀ) ማዳበሪያ የሚያመርት የሆነ እንደሆነ በማምረት ሥራ ላይ በቀጥታ የሚሠማሩ የሙያ ብቃትና ችሎታ ያላቸው ሠራተኞች ያሉት ፤

ለ) የሚያመርተው ማዳበሪያ ጥራትና የንጥረ ነገር ይዘት ደረጃው የጠበቀ ለመሆኑ ሙከራ (ፍተሻ) የሚያደርግበት ላቦራቶሪ ያለው ፣ መሆን ይኖርበታል ።

፮· ለብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለሚቀርብ ማመልከቻ

፩· በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማግኘት የሚቀርብ ማመልከቻ ለዚሁ ተግባር በተዘጋጀ ቅጽ ላይ ተሞልቶ ለኤጀንሲው መቅረብ አለበት ።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ ማዳበሪያ ወይም ድብልቅ ማዳበሪያ አምራች ከሆነ ፤

ሀ) በማምረት ሥራ ላይ በቀጥታ የሚሠማሩ ባለሙያዎችን የሙያ ብቃትና ችሎታ ፤

ለ) የሚያመርተው ማዳበሪያ ጥራትና ንጥረ ነገር ይዘት ደረጃውን የጠበቀ ለመሆኑ ሙከራ (ፍተሻ) የሚያደርግበት ላቦራቶሪ ማቋቋሙን

ኤጀንሲው ለዚሁ ተግባር ባዘጋጀው ቅጽ ላይ መሙላት አለበት ።

16) "Importer and/or Exporter" means a person who imports and/or exports fertilizer;

17) "Inspector" means an inspector of fertilizer assigned under Article 24 of this Proclamation.

18) "Ethiopian Standards" means fertilizer standards formulated by the quality and Standards Authority of Ethiopia;

19) "Licensing body" means as the condition requires Ministry of Trade and Industry of the Federal Government or the Regional Bureau of Trade and Industry or Bureau of trade and Industry accountable to the Federal Government or other appropriate Federal or Regional Body;

20) "Board" means as the condition requires, the National Fertilizer Industry Agency Board or the board of Quality and Standards Authority of Ethiopia;

21) "Agency" means the National Fertilizer Industry Agency;

22) "Authority" means the Quality and Standards Authority of Ethiopia.

3. *Scope of Application*

The Provisions of this Proclamation shall apply to a person who is engaged in the business of fertilizer.

SECTION TWO

*Competence Assurance Certificate*

4. *The Necessity of Competence Assurance Certificate*

Any person who wants to engage in fertilizer business shall possess a competence assurance certificate of the Agency.

5. *Conditions Enabling to Engage in the Fertilizer Business Sector*

1) Any person who wants to engage in fertilizer business shall possess competence assurance certificate, acquired by fulfilling the requirments of the Agency.

2) Notwithstanding sub-Article (1) of this Article

(a) where the applicant is a manufacturer of fertilizer, shall have qualified professional employees who have directly engaged in manufacturing.

(b) Where the applicant has established a laboratory wherein he tests the quality and the contents of substance of fertilizer he manufactures.

6. *Application for Competence Assurance*

1) Pursuant to Article 5 of this Proclamation an application to get competence assurance certificate shall be in-accordance with the form prepared for this pupose, and shall be given to the Agency.

2) Notwithstanding sub-Article (1) of this Article the Agency shall record in the form designed for this purpose:

(a) Qualification of the professional employees who directly engaged in manufacturing

(b) whether the applicant has established a laboratory wherein he tests the quality and the content of substance of fertilizer he manufactures.

፯· <u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የሚያስከትሉ ሁኔታዎች</u>

ኤጀንሲው በሚከተሉት ምክንያቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አይሰጥም ፡

፩· ቀደም ብሎ የነበረው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰረዘበትና ከተሰረዘበት አንድ ዓመት ያልሞላው ፤

፪· ይህ አዋጅ ከመውጣቱ በፊት በማዳበሪያ ንግድ ሥራ ጥፋት ፈጽሞ በሌላ ሕግ የተፈረደበትና ቅጣቱን ያልጨረሰ፣

፫· በዚህ አዋጅና በአንቀጽ ፭ የተደነገጉትን ያላሟላ፣

፬· ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም በወጣ ደንብ መሠረት የተፈረደ በትና ቅጣቱን ያልጨረሰ ።

፰· <u>ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማግኘት</u>

፩· የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ የጠፋበት ወይም የተበላሸበት ማንኛውም ሰው ለኤጀንሲው በጽሑፍ በማመልከት ምትክ ማግኘት ይችላል ።

፪· ምስክር ወረቀቱ የተበላሸበት ምትክ እንዲሰጠው ሲጠይቅ የተበላሸውን ይመልሳል ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ኤጀንሲው ምስክር ወረቀቱ የጠፋ መሆኑንና ምትክ እንዲሰጥ መጠየቁን የሚገልጽ የጋዜጣ ማስታወቂያ በአመልካቹ ወጪ እንዲወጣ ባደረገ በአንድ ወር ውስጥ ተቃዋሚ አለመቅረቡን በማረጋገጥ በደንቡ የተመለከተውን ክፍያ በማስከፈል ምትክ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል ።

፱· <u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ፀንቶ ስለሚቆይበት ጊዜ</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት የተሠጠ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለአንድ ዓመት የፀና ይሆናል ።

፲· <u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት እድሳት</u>

፩· የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ማንኛውም ሰው ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን ቅጽ ሞልቶ የምስክር ወረቀቱ የሚያገለግልበት ጊዜ ከማብቃቱ በፊት ባለው አንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለእድሳት ማመልከቻውን ለኤጀንሲው ማቅረብ አለበት ፡

፪· ኤጀንሲው የአመልካቹን ክንውንና ሌሎች አግባብ ያላቸውን ሁኔታዎች ከገመገመ በኋላ ማመልከቻው ከደረሰው በ፲፭ ቀን ውስጥ የአገልግሎት ዋጋ በማስከፈል የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ያድሣል ።

፲፩· <u>የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ስለማገድ ወይም ስለመ ሠረዝ</u>

፩· ኤጀንሲው በሚከተሉት ምክንያቶች የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀትን ሊያግድ ወይም ሊሠርዝ ይችላል ፡

ሀ) የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ያገኘው በማታለል ወይም የሀሰት መረጃ ወይም መግለጫ በማቅረብ ከሆነ ፤

ለ) ኤጀንሲውን ሳያስፈቅድ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ለሌላ ሰው ካስተላለፈ ፤

ሐ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ በተደነገገው መሠረት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን ካላሳደሰ ፤

መ) ማዳበሪያው የኢትዮጵያ የማዳበሪያ ደረጃ የጥራት መስፈርቶችን ያላሟላ ከሆነ ፤

(ሠ) የንግድ ፈቃዱ የተሠረዘበት ከሆነ ።

፪· ኤጀንሲው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱን እንደ ሠረዘ የንግድ ፈቃዱም እንዲሠረዝ ለፈቃድ ሰጪው ያሳውቃል ።

7. *Conditions for Refusal of Certificate of Competence*

The Agency shall not grant certificate of competence to a person:

1) Whose previous certificate of competence has been canceled and the period of cancellation has not elapsed one year;
2) Who has been convicted of an offense under other laws concerning fertilizer business prior to the issuance of this Proclamation;
3) Whose application is incomplete in respect to the provisions of Article 5 and of this proclamation;
4) Who has been convicted of an offense under this fertilizer proclamation or any other regulations thereunder and who hasn't completed his penalty.

8. *Obtaining Duplicate Copy of Certificate of Competence*

1) Any person whose certificate of competence is lost or deformed, may, on an application to the Agency in writing, can obtain duplicate copy of such certificate.
2) That such certificate is deformed, the deformed certificate should be returned.
3) The Agency subject to provision of sub-Article (1) of this Article upon publishing in newspaper notifies that the applicant certificate of competence is lost and requested duplicate copy of such certificate by the applicant's expense, may grant a duplicate copy within one month after notification, provided that no person has raised an objection to it.

9. *Period of Validity*

A certificate of competence granted under the provisions of this Proclamation shall be valid for a period of one year.

10. *Renewal*

1) Every holder of a certificate of competence desiring to renew the certificate, shall make an application to the Agency in accordance with the form designed for this purpose, within one month before the date of expiry of the said certificate.
2) On receipt of an application for renewal, and keep in view the performance of the applicant and other relevant circumstances and by charging service fee the Agency may renew the certificate of competence within 15 days period.

11. *Suspension or Cancellation of Certificate of Competence*

1) The Agency may suspend or cancel a certificate of competence on any of the following grounds:
   (a) That such certificate has been obtained by misrepresentation as to material particulars;
   (b) That such certificate has been passed over to any other person without prior permission of the Agency;
   (c) That such certificate has not been renewed pursuant to Article 10 of this proclamation;
   (d) That the fertilizer does not conform to the quality requirements of Ethiopian Standards on fertilizers;
   (e) That license for fertilizer business dealing has been canceled.
2) The Agency after having canceled the certificate of competence notify to the licensing Authority to cancel the license.

፲፪· <u>መረጃ ስለማቅረብ</u>

በማዳበሪያ የንግድ ሥራ የተሠማራ ማንኛውም ሰው ኤጀንሲው መረጃ በሚጠይቅበት ወቅት በተዘጋጀው የመረጃ መሰብሰቢያ ቅጽ ላይ የተጠየቀውን መረጃ ሞልቶ የማቅረብ ግዴታ አለበት ።

## ክፍል ሦስት
## ስለ ማዳበሪያ አመራረት ፣ ንግድ ፣ አያያዝና ሥርጭት

፲፫· <u>ማዳበሪያ ስለማምረት ፣ ወደ ሀገር ውስጥ ስለማስገባት እና ስለ ማሰራጨት</u>

በሀገር ውስጥ ተመርቶም ሆነ ከውጭ አገር መጥቶ የሚከማች የሚሠራጭና ለሽያጭ የሚቀርብ ማንኛውም ማዳበሪያ ፤

፩· የኢትዮጵያ ደረጃዎችን ያሟላ ፤ እና

፪· በሀገሪቱ ውስጥ በማዳበሪያነቱ በጥቅም ላይ እንዲውል በኤጀንሲው የተመዘገበ ፣ መሆን አለበት ።

፲፬· <u>ክልከላ</u>

፩· ማንኛውም ሰው ከኤጀንሲው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ሳይሰጠውና ከምስክር ወረቀቱ ግዴታ ውጭ ማንኛውንም ማዳበሪያ ማምረት አይችልም ።

፪· ማንም ሰው በኢትዮጵያ ደረጃ ወይም የኢትዮጵያ ደረጃ በማይገኝበት ጊዜ በኤጀንሲው ያልተወሰነ ማንኛውም ማዳበሪያ ፣ የማዳበሪያ ድብልቅ ወይም ልዩ ድብልቅ በተሰጠው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተወሰኑት ዝርዝሮች ጋር በማይስማማ ሁኔታ ከውጭ ማስገባት ፣ ለሽያጭ ማምረት ወይም መሸጥ ፣ ለሽያጭ ማቅረብ ወይም ለሽያጭ ማሳየት ወይም ማከፋፈል አይችልም ።

፫· ማንም ሰው የሚከተሉትን መሸጥ ፤ ለሽያጭ ማቅረብ ፤ ወይም ለሽያጭ ማሳየት ወይም ማከፋፈል አይችልም ፤

ሀ) ሌላ ማዳበሪያ የሚሰጥበትን ስም በማስመሰል ወይም በመተካት የተዘጋጀ ማንኛውም ማዳበሪያ፤

ለ) የተበከለ ማንኛውም ማዳበሪያ ፤

ሐ) የሀሰት ወይም የሌላውን ግል ድርጅት ወይም ኩባንያ ማዳበሪያ የሚያመርት በማስመሰል ምልክቱ ወይም መያዣው ይህንኑ የሐሰት ወይም የሌላ ድርጅት ወይም ኩባንያ ስም የያዘ ማንኛውም ማዳበሪያ ፤

መ) ምልክቱ ወይም መያዣውን በሐሰት የራስ በማስመሰል አሳሳች መረጃ የሚሰጥ ማንኛውንም ማዳበሪያ ።

፬· ማንኛውም ሰው የተፈጥሮ ማዳበሪያ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ ማስገባት አይችልም ።

፲፭· <u>ስለማዳበሪያ ማሸጊያ ፣ ስለአስተሻሸግና ምልክት አደራረግ</u>

፩· የማዳበሪያ ማሸጊያ ከረጢት ስሪትና በከረጢቱ ላይ መደረግ ያለባቸው ምልክቶች የኢትዮጵያ ያስተሻሸግና ምልክት አደራረግ ደረጃን ያሟሉ መሆን አለባቸው ።

፪· በኢትዮጵያ ደረጃ ማሸጊያ ከተደነገገለት ውጪ የሆነ የማዳበሪያ ዓይነት ከውጪ ሀገር ሲመጣ ወይም ከሀገር ሲመረት መያዣው ፕላስቲክ ወይም ጣሳ ከሆነ ማሸጊያው ተፈላጊውን መረጃ የያዘ መሆን አለበት ።

፲፮· <u>በከረጢት ያልታሸገ ማዳበሪያ ስለመሸጥ</u>

የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ፤

፩· የማዳበሪያ ችርቻሮ ነጋዴ በማንኛውም ሰዓት ከእያንዳንዱ የማዳበሪያ ዓይነት አንዳንድ ከረጢት ያልታሸገ ማዳበሪያ ለሽያጭ ሊይዝ ይችላል ።

12. *Duty to Provide information*

Any person engaged in the activity of fertilizer sector shall have the duty to provide information relating to fertilizer in accordance with the form designed for collecting information whenever requested by the Agency.

## SECTION THREE
## *Manufacturing, Dealing, Handling Distribution of Fertilizer*

13. *Manufacture, Import and Distribution of Fertilizer*

Any fertilizer manufactured locally or imported and stocked, which is ready for distribution and sale:

1) Shall conform to the requirements of Ethiopian Standards,
2) Shall be registered by the Agency for use in the country as fertilizer.

14. *Restriction*

1) No person shall carry on the activity of preparing any fertilizer, without certificate and outside of the terms and conditions of such certificate of manufacture granted to him by the Agency.
2) No person shall import, manufacture for sale or sell, offer for sale, or exhibit for sale or distribute any fertilizers, mixture or special mixture of fertilizers, which does not conform to the particulars specified in the competence assurance certificate and which does not conform to the Ethiopian standard and in the absence of such standard unless authorized by the Agency.
3) No person shall sell, offer for sale, or exhibit for sale or distribute:
   (a) Any fertilizer which is an imitation or a substitute for another fertilizer under the name of which it is sold;
   (b) Any fertlizer found to be adulterated,
   (c) Any fertilizer, label or container whereof bears the name of any individual firm or company purporting to be manufacturer of the fertilizer, which individual firm or company does not exist.
   (d) Any fertilizer label or container wherof bears any statement which makes a false claim or gives misleading information.
4) No person shall import natural fertilizer.

15. *Package, Packing and Labeling of Fertilizer*

1) Packaging materials for fertilizer bags and labels affixed on bags shall comply with the relevant Ethiopian standards.
2) Types of fertilizer locally manufactured or imported, not in accordance with the Ethiopian standards for packaging contained in plastic or tin packages shall bear necessary informations.

16. *Selling Unpacked Fertilizer*

Notwithstanding the provisions of this Proclamation:

1) Fertilizer retailer can maintain one bag of unpacked fertilizer of each type of fertilizer at anytime, for sale.

፪· ማንኛውም ማዳበሪያ አምራችና አስመጪ ለድብልቅ ፤ ለልዩ ድብልቅና ለውህድ (ዝንቅ) ማዳበሪያ አምራችና ለሰፋፊ እርሻዎች ብቻ ያልታሸገ ማዳበሪያ ሊሸጥ ይችላል።

፲፯· <u>ደረጃ ያላሟላ ማዳበሪያ ስለመሸጥ</u>

፩· የዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነው ማንኛውም ሰው ማንኛውንም ያልተበከለ ነገር ግን ከኢትዮጵያ ደረጃዎች ዝቅ ያለ ማዳበሪያ በሚከተሉት ሁኔታዎች መሸጥ ፤ ለሽያጭ ማቅረብ ፤ ማከማቸት ፤ ለሽያጭ ማሳየት ወይም ማከፋፈል ይችላል ፤

ሀ) ደረጃ ባላሟላው ማዳበሪያ ከረጢት ላይ በቀይ ቀለም በጉልህ የኢትዮጵያ ደረጃ ያላሟላ የሚሉ ቃላትና X ምልክት የተደረገ እንደሆነ ፤

ለ) ደረጃ ያላሟላ ማዳበሪያ የሚሸጠው ለድብልቅ ወይም ልዩ ድብልቅ ማዳበሪያ አምራቾች ፤ ለእርሻ ምርምር ተግባር ፤ ለግብርና ቢሮዎች ፤ ለእርሻ ምርምር ተቋማት ፤ ለዩኒቨርስቲዎችና ኮሌጆች ብቻ የሆነ እንደሆነ እና ፤

ሐ) ደረጃውን ያላሟላ ማዳበሪያ ለመሸጥ ከኤጀንሲው አስቀድሞ ፈቃድ የተገኘ እንደሆነ ።

፪· ኤጀንሲው ደረጃ ያላሟሉ ማዳበሪያ የፍተሻ ውጤት ሲደርሰው በንጥረ ነገሩ ይዘት መጠን የመሸጫ ዋጋውን ይወስናል ።

፲፰· <u>የተበከለ ማዳበሪያን ስለማስወገድ</u>

ማንኛውም ማዳበሪያ የተበከለ መሆኑ ከተረጋገጠ ኤጀንሲው በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በጥቅም ላይ እንዳይውል ይወገዳል ።

፲፱· <u>የማዳበሪያ አቅርቦትና ስርጭት</u>

፩· ማንኛውም አስመጪ ማዳበሪያ የሚገዛበትን ፤ ወደብ ላይ የሚያደርስበትንና ከወደብ በማንሳት የሚያጓጉዝበትን የጊዜ ሰሌዳ ለኤጀንሲው የማሳወቅ ግዴታ አለበት ።

፪· ማንኛውም አስመጪ ያስመጣውን ማዳበሪያ በሰጠው የጊዜ ሰሌዳ መሠረት ከወደብ ወደ መሀል አገር ማጓጓዝ አለበት ።

፫· ማንኛውም አስመጪ ፤ የጅምላና ችርቻሮ ነጋዴ የያዘውን ማዳበሪያ ለተጠቃሚ በሚፈለገው ወቅትና ቦታ ለሽያጭ ማቅረብ አለበት ።

፳· <u>ስለፈቃድ አሰጣጥ</u>

፩· ማዳበሪያ ለማምረት ፤ ለማስመጣት ፤ በጅምላና በችርቻሮ ለመነገድ ማመልከቻ ለፈቃድ ሰጪው ሲቀርብ ብለት አመላካቹ ከኤጀንሲው የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት የተሰጠው ለመሆኑ ፈቃድ ሰጪው ማረጋገጥ አለበት ።

፪· የምርምር ተቋማት ምርምር ለማካሄድና በግብርና ሥራ ላይ የተሰማሩ ኢንቨስተሮች በራሳቸው እርሻ ላይ ለራሳቸው አዳዲስ የማዳበሪያ ዓይነቶችን ለማስገባት ሲፈልጉ ከኤጀንሲው ፈቃድ ማግኘትና ስለአገባባቸው ኤጀንሲው ያወጣውን መመሪያ መከተል አለባቸው ።

፫· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ፈቃድ ያገኘበትን ማዳበሪያ ለሌላ ማንኛውም ሰው አሳልፎ መስጠት ወይም መሸጥ አይችልም ።

2) *Any fertilizer manufacturer and importer can sale unpacked fertilizer only to manufacturers of mixture of fertilizers, special mixture of fertilizer and composite mixture of fertilizers and to large scale farms.*

17. *Selling of sub-Standard Fertilizer*

1) Notwithstanding the provisions of this Proclamation, any person, can sell, offer for sale, stock, exhibit for sale or distribute any fertilizer which, not being an adulterated fertilizer, does not confirm to the Ethiopian standard, subject to the condition that :

(a) the container to such sub-standard fertilizer is conspicuously superscribed in red colour with the words,, "sub-standard" and also with sign "X":

b) sub-standard fertilizer shall be sold only to the mixture of or special mixture of fertilizers manufacturer, for agricultural research purpose to the Agricultural bureaus, Agricultural research institutes, universities and colleges; and

(c) sub-standard fertilizer shall be sold upon prior authorization of the Agency.

2) the Agency, upon receipt of the test result of sub-standard fertilizer, shall fix the prices, as per size of the content of the substance.

18. *Disposal of Adulterated Fertilizer*

Any adulterated fertilizer shall be disposed in accordance with the Agency directives.

19. *Supply and Distribution of Fertilizer*

1) Any importer of fertilizer is liable to notify the Agency the schedule of purchase, freightage at port and transportation of fertilizer from the port.

2) Any importer of fertilizer shall transport fertilizer to the center of the country within the period of notified schedule.

3) Any importer, wholesaler and retailer shall supply the fertilizer to the consumer at the required time and place for sale.

20. *Licensing*

1) The licensing Authority upon receipt of application for license to manufacture, import, wholesale and retail of fertilizer, shall ascertain that the applicant has obtained a competence assurance certificate from the Agency.

2) Research institutes and investors that require to import new types of fertilizer for use respectively in research purposes and in their own farms, shall obtain permission from the Agency, and shall be subject to the specified directive of the Agency.

3) Any person who obtains a permission pursuant to sub-Article (2) of this Article, shall have no right to pass over or sell the fertilizer to any person.

## ክፍል አራት
## አስፈጻሚ መሥሪያ ቤቶችና የሥራ ድርሻቸው

### ፳፩· የባለሥልጣኑ ተግባርና ሃላፊነት

ባለሥልጣኑ በመቋቋሚያ ሕጉ የተሰጡት ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቁ ሆኖ ፤ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባር ይኖሩታል ፤

፩· ከኤጀንሲው በሚቀርብለት የተፈላጊ ማዳበሪያ ዓይነት ዝርዝር መሠረት ከውጪ የሚገቡ ማዳበሪያዎችን ይመረምራል ፤ ጥራታቸውን ያረጋግጣል ፤

፪· የዚህ አዋጅ አንቀጽ (፳፪) እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ የሀገር ውስጥ ማዳበሪያ አምራቾች የሚያመርቱት ማዳበሪያ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ መሆኑን ያረጋግጣል ።

### ፳፪· የኤጀንሲው ተግባርና ሃላፊነት

ኤጀንሲው በማቋቋሚያ ሕጉ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ ፤

፩· ወደሀገር ውስጥ የሚገቡትንም ሆነ በሀገር ውስጥ የሚመረቱትን የማዳበሪያ ዓይነቶች ይወስናል ፤

፪· የማዳበሪያ ዓይነቶች በህዝብ ማስታወቂያ እንዲወጡ ያደርጋል ፤ ይከታተላል ፤ ይቆጣጠራል ፤ ዝርዝራቸውንም በየጊዜው ለባለሥልጣኑ ይገልጻል ፤

፫· ማዳበሪያ ማምረት ፤ ማደባለቅ ፤ ማስመጣት ፤ በጅምላና በችርቻሮ መሸጥን በተመለከተ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሰጣል ፤ ያድሳል ፤ ያግዳል ፤ ይሰርዛል ፤

፬· ይህን አዋጅ ለማስፈጸም የኢንስፔክሽን ቡድን አቋቁሞ ኢንስፔክተሮችን ይመድባል ፤ ላቦራቶሪዎችን ያቋቁማል ፤ ያደራጃል ፤ ያስተዳድራል ፤ የማዳበሪያ ጥራትን ይመረምራል ፤ ይቆጣጠራል ፤

፭· ዋጋን ለማረጋጋት ስልት ይቀይሳል ፤ ተግባራዊነቱን ይከታተላል ፤ ይቆጣጠራል ፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘውም መወሰድ ስለሚገባቸው እርምጃዎች አጥንቶ ለመንግሥት ሀሳብ ያቀርባል ፤ ሲወሰንም ተግባራዊነቱን ይከታተላል ፤

፮· ማዳበሪያ ለየሰብል ዘመኑ በሀገሪቱ ውስጥ በበቂ መጠን መቅረቡንና ወደ ክልሎች በወቅቱ መሠራጨቱን ይከታተላል፤ ይቆጣጠራል ፤

፯· ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ሥልጣኑን በውክልና ለመስጠትና ውክልናው ተፈጻሚ የሚሆንባቸውን ሁኔታዎች ለመወሰን ይችላል ፤

፰· ማዳበሪያ እንዳይሸጥ ሲታገድ በላቦራቶር ምርመራ ውጤት ላይ በመመርኮዝ ውሳኔ ይሰጣል ፤

### ፳፫· የኢንስፔክተር ተግባርና ሃላፊነት

ኢንስፔክተሩ በኤጀንሲው የሚመደብ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ሃላፊነት ይኖሩታል ፤

፩· በማምረት ፤ በክምችት ፤ በሽያጭ ላይ ወይም በማንኛውም ሁኔታ ስለሚገኝ ማንኛውንም አምራች ፣ አስመጪ፣ ጅምላ ነጋዴ ፣ ወይም ችርቻሮ ነጋዴ መረጃ ይጠይቃል ፤

፪· አግባብ ባላቸው የኢትዮጵያ ደረጃዎች በተገለጸው መሠረት የማዳበሪያ ናሙናዎች ይወስዳል ፤ በሦስት ቅጅ የናሙና አወሳሰድ ዝርዝር አዘጋጅቶ ከእያንዳንዱ ቅጅ ጋር የታሸጉና ልዩ ምልክት የተደረገባቸው ናሙናዎች በማቀናጀት አንድ ቅጅ ለነጋዴው ፣ አንድ ቅጅ ለላብራቷር ምርመራ ፣ ሦስተኛውን ቅጂ ከሱ ቀጥሎ ላለው ከፍተኛ ባለሥልጣን ያቀርባል ፤

## *SECTION FOUR*
## *Enforcement Bodies and their Duties*

### 21. Duties and Responsibilities of the Authority

Notwithstanding the powers it is vested with under its establishment proclamation, the Authority, shall have the following powers and duties:

1) The Authority on the basis of the essential type of fertilizers list provided by the Agency shall carry out inspection on imported fertilizers and certify the quality of same;
2) Notwithstanding to the provisions of Article 22(4) of this Proclamation, ensure that locally manufactured fertilizer comply to the quality requirement of the specified standard.

### *22. Duties and Responsibilities of the Agency*

Notwithstanding the powers it is vested with under its establishment proclamation, the Agency shall:

1) decide the type of fertilizers to be imported or locally manufacured;
2) enable the issuance of the types of fertilizer in public notification, make follow-up, monitor and periodically notify same to the Authority;
3) grant, refuse, renew, suspend, cancel competence assurance certificate in matters related to manufacture fertilizer, mixture of fertilizer, import, wholesale and retail of fertilizer;
4) establish a team of inspection, assign inspectors, establish, organize and administer laboratories to enforce this proclamation; perform quality control and testing activities on fertilizer;
5) design strategies to establish price, follow-up the enforcement of the strategies and monitor same, whenever required, study appropriate measures to be taken and initiate ideas of the same to the government; and follow-up the practicability, upon decision;
6) follow-up and monitor the supply of fertilizer every cropping season in adequate quantity into the country and its timely distribution to the regions;
7) may delegate its power and decide upon the conditions on how to exercise the delegation to enforce this proclamation;
8) decide upon suspension of fertilizers from sell pursuant to the laboratory test result.

### *23. Duties and Responsibilities of the Inspector*

An inspector shall be assigned by the Agency and has the following duties and responsibilities:

1) require any manufacturer, importer, wholesale, or retail dealer involved in fertilizer business to give any information in his possession with respect to manufacture, storage and selling of any fertilizer manufactured or in any manner handled by him;
2) draw fertilizer samples according to procedure described in the relevant Ethiopian standard; provided that inspector shall prepare sampling details together with packed and specially labeled samples in triplicate, and hand over one to the dealer, send one to the laboratory for analysis and the third to his next higher authority.

፫· ማንኛውም ማዳበሪያ በዚህ አዋጅ ድንጋጌ መሠረት በትክክል መመረቱን ወይም በመመረት ላይ መሆኑን ፣ መሸጡን ፣ ለሽያጭ መቅረቡን ፣ መከማቸቱን ፣ ለሽያጭ መታየቱን ወይም መከፋፈሉን ለማረጋገጥ በቦታው ተገኝቶ ይፈትሻል ፣

፬· የማንኛውም ማዳበሪያ ሥራ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) የተዘረዘሩትን ሥራዎች በሚጥስ ሁኔታ መከናወኑን ፣ እየተከናወነ መሆኑን ወይም ሊከናወን መታቀዱን የሚያሳምን ምክንያት ካጋጠመው ማዳበ ሪያው እንዳይሸጥ ማገድ ይችላል፣

፭· ኢንስፔክተሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) መሠረት ላገደው ማዳበሪያ በጽሁፍ የሽያጭ ማገጃ ማስታወቂያ ሰጥቶ የእገዳውን ምርመራ ውጤት ለኤጀንሲው ያሳውቃል ፣

፮· ማንኛውም የማዳበሪያ አምራች ፣ አስመጪ ፣ የጅምላና የችርቻሮ ነጋዴ በእጁ የሚገኘውን ማዳበሪያ አለአግባብ በማከማቸት ሰው ሰራሽ እጥረት እንዳይፈጠር ይከታ ተላል ፣ ይቆጣጠራል ።

## ክፍል አምስት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፳፬· <u>የመተባበር ግዴታ</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት ኢንስፔክተሩ ተግባሩን ማከናወን እንዲችል የሚመለከተው ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት ።

፳፭· <u>ስለ አቤቱታ አቀራረብ</u>

በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወስዳቸው እርምጃዎች ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ፣

፩· የኤጀንሲውን የሥራ ድርሻ በተመለከተ ለኤጀንሲው የሥራ አመራር ቦርድ ፣

፪· የባለሥልጣኑን የሥራ ድርሻ በተመለከተ ለባለሥ ልጣኑ የሥራ አመራር ቦርድ ፣ አቤቱታ ማቅረብ ይችላል ።

፳፮· <u>ስለ ቅጣት</u>

፩· ሆን ብሎ የተበከለ ማዳበሪያ ወይም ያልተመዘገበ ማዳበሪያ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የሸጠ ማንኛውም ሰው ከ፰ ዓመት ባላነሰና ከ፲ ዓመት ባልበለጠ የእሥራት ቅጣትና ከብር ፳፭ ሺህ በማያንስና ከብር ፴፭ ሺህ ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል ።

፪· በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፲፯ ከተደነገገው ውጭ የኢትዮ ጵያን ደረጃዎች ያላሟላ ማዳበሪያ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የሸጠ ማንኛውም ሰው ከ፭ ዓመት ባላነሰና ከ፯ ዓመት ባልበለጠ የእሥራት ቅጣትና ከብር ፳፭ ሺህ ባላነሰና ከብር ፴ ሺህ ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል ።

፫· የከረጢት ስሪት ደረጃውን ያልጠበቀ መሆኑን እያወቀ በተጠቀሰው ከረጢት ማዳበሪያን ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የሸጠ ማንኛውም ሰው ከ፫ ዓመት ባላነሰና ከ፭ ዓመት ባልበለጠ የእሥራት ቅጣትና ከብር ፲፭ ሺህ በማያንስና ከብር ከ፳፭ ሺህ በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል ።

፬· በከረጢቱ ላይ የምልክት አደራረጉና የከረጢቱ አስተ ሻሸግ ደረጃውን ያልጠበቀ ፣ በከረጢቱ ውስጥ ያለው የማዳበሪያ ክብደት መጠን ከተከፈለበት ዋጋ ያነሰ ማዳበሪያ ሆን ብሎ ለሽያጭ ያቀረበ ወይም የሸጠ ማንኛውም ሰው ከ፩ ዓመት ባላነሰና ከ፫ ዓመት ባልበለጠ የእሥራት ቅጣትና ከብር ፭ ሺህ ባላነስና ከብር ፲፭ ሺህ ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል ።

3) enter and search any premises where any fertilizer is manufactured or being manufactured, sold, offered for sale, stored, exhibited for sale or distributed according to the provisions of this proclamation;

4) seize or detain fertilizer in respect of which he has reason to believe that a contravention of sub-Article (3) of this Article has been, is being or is about to be committed;

5) pursuant to sub-Article (4) of this Article, the Inspector shall give the stop sale notice in writing to the person whose stocks have been detained and initiate appropriate action and notify the Agency;

6) follow-up and monitor every manufacture, importer, wholesaler and retail dealer of fertilizer of his possession, to protect a man-made shortage of fertilizer through hoarding fertilizer stock.

## *SECTION FIVE*
## *Miscellaneous*

24. *Duty to Co-operate*

Any person, if so required by an Inspector shall be bound to afford all necessary facilities to him for the purpose of enabling him to exercise his duties under this proclamation.

25. *Appeal*

Any person who is aggrieved by the action taken according to this Proclamation can appeal:

1) in respect of duties of the Agency, to the Management Board of the Agency;

2) in respect of duties of the Authority, to the Management Board of the Authority.

26. *Penalties*

1) Any person who intentionally offers for sale or sales adulterated or unregistered fertilizers will be punished with imprisonment from 8 years upto 10 years and with fine from Birr 25 thousands up to 35 thousands.

2) Any person who offers for sale or sells sub-standard fertilizer in contravention to Article 17 of this proclamation will be punished with imprisonment from 5 years upto 7 years and with fine from Birr 25 thousands upto 30 thousands.

3) Any person who knowingly offers for sale or sells fertilizers in bags which do not comply with the standard will be punished with imprisonment from 3 years upto 5 years and with fine from Birr 15 thousands upto 25 thousands.

4) Any person who offers for sale or sells fertilizers in bags which do not comply with the standard on labeling and packaging and reduces the required content of the bag, will be punished with imprisonment from 1 year upto 3 years and with fine from Birr 5 thousands to 15 thousands.

፭· የኤጀንሲው ኢንስፔክተር ወይም ሠራተኛ በዚህ አዋጅ መሠረት ሥልጣንና ተግባሩን ለመወጣት ማስረጃ ሲጠይቅ ለመተባበር ፈቃደኛ ያልሆነ ማንኛውም ሰው ከ፩ ዓመት በማይበልጥ የእሥራት ቅጣትና ከብር ፭ ሺህ ባላነሰና ከብር ፲ ሺህ ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል ።

፮· ኢንስፔክተሩን ያሳሳተ ወይም ያታለለ ፤ የተወሰደ ናሙና ወይም ለምርመራ የተሰጠ ናሙና በትክክል ምርቱን እንዳይወክል ሆን ብሎ ያዛባ ማንኛውም ሰው ከ፩ ዓመት ባላነሰና ከ፫ ዓመት ባልበለጠ የእሥራት ቅጣትና ከብር ፲ ሺህ ባላነሰና ከብር ፲፭ ሺህ ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል ።

፯· ሆን ብሎ የታሸገ መጋዘን የከፈተ ማንኛውም ሰው እስከ ፩ ዓመት በሚደርስ የእሥራት ቅጣት ወይም ከብር ፭ ሺህ ባላነሰና ከብር ፲ ሺህ ባልበለጠ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

## ፳፯· ደንብ የማውጣት ሥልጣን

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል ።

## ፳፰· መመሪያዎች

ኤጀንሲው ይህን አዋጅ ተግባራዊ ለማድረግ የሚረዱ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል ።

## ፳፱· የሌሎች ሕጎች ተፈጻሚነት

፩· የኢንቨስትመንት እንዲሁም የንግድ ምዝገባና ቁጥጥር ሕጎች በማዳበሪያ ንግድ ሥራ በተሠማራ ሰው ላይ እንደ አግባቡ ተፈጻሚ ይሆናሉ ።

፪· ማንኛውም ሌላ ሕግ ወይም የተለመደ አሠራር ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ሆኖ ካልተገኘ በቀር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል ።

## ፴· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም· ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ፤ ኅዳር ፲፭ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ·ም·

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

5) Any person who prohibits document, when requested by an inspector of the Agency or worker in the exercises of his power and duties will be punished with imprisonment upto 1 year and with fine from Birr 5 thousands upto 10 thousands.

6) A person who deceives or misleads the inspector, tampers with an article in a way that a sample of it, taken or submitted for analysis, incorrectly represents the articles, will be punished with imprisonment from 1 year upto 3 years and with fine from Birr 10 thousands upto 15 thousands.

7 A person who intentionally break a sealed store will be punished with imprisonment upto 1 year and with fine from Birr 5 thousands upto 10 thousands.

## 27. *Power to Issue Regulations*

The council of Ministers shall may issue regulations in order to implement this Proclamation.

## 28. *Directives*

Inorder to implement this Proclamation the Agency may issue directives.

## 29. *Laws Consistent to this Proclamation*

1) As the condition requires, the Investment and Commercial Registration and Business Licensing proclamation will be applicable to a person engaged in fertilizer business.

2) Other law or customary practice which is consistent with this Proclamation shall have effect with respect to matters covered by this Proclamation.

## 30 *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 24th day of November, 1998.

Done at Addis Ababa, this 24th day of November, 1998.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA